**"ከሞቱት ያልሞትነው!"**

**April 23, 2015**

"

**.....** *የለቅሶና የብዙ ዋይታ ድምፅ በራማ ተሰማ፤ ራሔል ስለ ልጆችዋአለቀሰች፤ ልጆችዋ ስለሞቱባት መጽናናት እምቢ አለች።....*" /ማቴዎስ **2፡18**/



አድማ በታኝ ፖሊሶች ህዝቡን እያባረሩ

*ኮንፊሽየስ ወደ ጫከ በመሄድ ግዜውን ማሳለፍ ይወድ ነበር ይባላል።ከዕለታት አንድ ቀን እንደተለመደው ወደ አንድ፤ ከአካባቢው 'ርቆወደሚገኝ ጫካ አመራ። ከሰዓታት ጉዞ በኋላ ጥቅጥቅ ባል ጫካ ውስጥእንደደረሰ ለማርፍ ሲሞክር የገጠመው፤ የተለመደው የወፎች ዝማሬናየአበባወችና የዛፎች ውብ ማዕዛ ሳይሆን እጅግ አሳዛኝ ፣ የለቅሶና የሲቃድምጽ ነበር። ኮንፊሽየስ የሰማውን ማመን እያቃተው ወደዚያው አመራ፤ወደ ድምጹ እየተጠጋ ሲሄድ፤ አንዲት ሴት ሳሩን እየነጬች መሬቱንእየቧጨረች የ "ኤሎሄ" ዋይታ ታስተጋባለች። ራሱን ለመቆጣጠርእየሞከረ ቀስ እያለ ተጠጋት። ሊያጽናናትም ሞከረ። ግን የምትጽናና ሴትሁና አላገኛትም። ይሁን እንጂ በዚህ ጫካ ውሰጥ ለምን እንደመጣችናየዋይተዋን ምክንያት እ'ድትነግረው አግባባት። እሷም ከአንድ ልጇ ጋርወደዚህ ጫካ ለመኖር እንደመጣችና ልጇ ግን በአውሬዎች እንደተበላባት ቋንቋ ሊገልጸው በማይችል ሀዘን ነገረችው። " አውሬዎች አንድ ልጃን ብሉት።"*

*ኮንፊሽየስም በመገረም "ለምን ከተማ ውስጥ አትኖሩም ነበር? እንዴት ጫከ ወስጥ መኖር ትመርጣላችሁ? " በማለት ጠየቀ። ያገኘው መልስ ግን " ጌታዬከተማ ያሉት አውሬዎች ከዚህ ጫካ ውስጥ ካሉት አውሬዎች ይብሳሉ፤ የከተማዎቹ አውሬዎች ባሌንና ታላቁን ልጅን በልተዋል፤ የቀረኝን አንድ ልጅንለማትረፍ ነበር ወደዚህ ጫካ የመጣውት፤ ይኸው እሱንም አጣውት።" አለችው።*

*እኛም ከወያኔ አውሬዎች የተርፉትን ወገኖቻችን በጫካ አውሬዎችአስበላናቸው፣ አሰየፍናቸው።*

ግን እኛ **"**ያልሞትነው**"** በህይወት ያለነው ምን እያደረግን ነው**?** አሁንም እንዳለፈ ሁሉ **"**መግለጫ እናወጣለን**!.....** ሻማ እናበራለን**!.......** ሰላማዊ ሰልፍ እንወጣና፣ ድርጊቱን እናወግዛለን**!.......** ወያኔ ወገኖቻችን ይታደግ እንላለን **(**ሃያ አራት ዓመት ሙሉ**) ......**ወያኔ ደግሞ ቆመጡን ያቀምሰናል፤ ጥይቱን ያጠጣናል፤ እስርቤት ያጉረናል፤ በባዕድ ሀገር እየሄድን እንድንታረድ፣ ከሳኡዲ እስከ የመን፣ ከደቡብ አፍሪካ እስከ ሊቢያ፣ ከሳሀራ እስከ ካለሀሪ በርሃ ፣ ከኤደን እስከ ሜድትርራያን ባህር ብሎም ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚል ዜጋ እስከ አለበት ድረስ ባህር፣ እሳት፣ በርሃና ሰይፍ እንዲበላን ያመቻችናል።

የገዛ ሀገራችን ለወያኔ አውሬዎች አስረክበናልና፤ መንግስትና ሀገር እስከሌለን ድረስ በየትም ቦታ ብንሄድ የሚጠብቀን በባዕዳን አውሬዎች እጅ መውደቅና መታረድ ነው። ኮንፊሽየስ ጫካ ውስጥ እንዳገኛት እናት።

ከዚህ ላይ ከዚህ በፊት የጦመርኩትን በከፊል በድጋሜ ልጠቀም፤

" ዓለም የም'ጠፋው፣ ሰይጣናዊ ምግባር በሚፈጽሙ ሳይሆን፤ ምንም ሳያደርጉ ቀጭ ብለው በሚመለከቷቸው ሰዎች ነው።" /አልበርት አነስታየን/

እናም የምድርን የሰቆቃና የሞትን አይነት ሁሉ እያስከፈሉን፣ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊያንን እያጠፉ ያሉት፣ እስላማዊ መንግስት ነኝ ባይ **(**አይሲኤል**)** ፣ ወያኔ፣ ሳኡዲ አረቢያ/ አረቦች፣ ምእራቡ ዓለም፣ ደቡብ አፍሪካ ወይም ሌላ ሳይሆን፣ እኛ እራሳችን ቁጭ ብለን የምንመለከተው ወይም ለታይታ የምንታይው፣ ኢትዮጵያዊያኖች ነን። እኛ ነን**.....** በሀያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ላይ ተቀምጠን፤ ለወገኖቻችን መሆን ያልቻልነው። እኛ ነን**.....** ለጠባብ መንደርተኞች ሀገራችን አሳልፈን

የሰጠን። ትላ'ትናም ይሁን ዛሬ እውነቱ ይኸው ነው። ይኸን እውነታ ተቀብለን፣ በተለይም በዚች ወቅት ለጎልውናችን ስንል የሚጠይቀውን መሰዋእትነት እስከ አልከፈልን ድረስ፣ ስቃይና ሰቆቃ፤ እንደ በግ መታረድ፣ እንደትላ'ቱና እንደዛሬው ሁሉ፣ ነገም ተባብሶ ይደገማል።

ባለፉት ዓመታት ከሀገርቤት ጀምሮ በዓለም ዙሪያ እንደ ቅጠል የረገፉትንና  የምድራችንን ስቃይ የከፈሉትን ለግዜውም ቢሆን ወደ ጎን ትተን፤ እስቲ ለደቂቃ የአይሲኤል ሰይፍ የበላቸውን ወግኖቻችን የመጨረሻ ሰዓት እናስበው**?** ሀዘን፣ **...**ለቅሶ፣ **....**ምን ይበቃል**?** ዋይታችንን የሚገልጽ ቋንቋ በዚች ምድር ላይ ይኖር ይሆን**?** ጎሊናችን ምን ይለናል**? "** ከሞቱት ላልሞትነው**"** ለኛ ለቀሪዎቹ ሸክሙ አይከብድም**? "**ሰው ከንቱ ነውና**......"** እንደ ትላንትናዎቹ  ወግኖቻችን ነገም እነዚህን እንረሳቸው ይሆን**?** በየትም ቦታና በማንኛውም ግዜና ሁኔታ ብንሆን ፣ በህይወት ላለን ዜጎች የማናመልጠው ነገር ፤ እነሱ የሰማዕትነትን አክሊል ተቀናጅተው ፤ የቤት ስራውን ለኛ ጥለውልን ሄደውል።

**———//———**

ፊልጶስ / ሚያዚያ **2007**
ኢ**-**ሜል**- philiposmw@gmail.com**